





# KrFን ለመምረጥ ፲ ምክንያቶች

## KrF ፡ ለሰብአዊ ክብር በአንድነት

1. **ዘላቂ እሴቶች**
   KrF ኖርዌይ የተመሰረተችበትን እሴቶች መጠበቅ ይፈልጋል ምክኒያቱም እነዚህ እሴቶች በቀላሉ ሊሸረሸሩ አይችሉም። መነሻችንን ካወቅን ፣ ከአዳዲስ ሰዎች እና ባህሎች ጋር በምንገናኝበት ጊዜ ይበልጥ እንተማመናለን። ሰብአዊ ክብር ፣ በጎ አድራጎት እና መጋቢነት የወደፊቱን ጊዜ ለመገንባት የሚያስችሉ እሴቶች ናቸው።

2. **ጊዜ እና የመምረጥ ነፃነት ለቤተሰብ**
   KrF ትናንሽ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች የሰጠው ምላሽ ግልፅ ነው ፡ ተጨማሪ ጊዜ እና የበለጠ የመምረጥ ነፃነት። ወሰን ያላቸው መፍትሄዎችን መቀነስ። ቤተሰቦች ሊጠናከሩ እንጂ በቁጥጥር ሊተዳደሩ አይገባም። KrF ለቤተሰቦች የመምረጥ ነፃነትን መስጠት ይፈልጋል ፣ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ እና ለልጆቹ የሚስማማውን መፍትሄ መምረጥ ይችላል።

3. **ለእድሜ ተስማሚ የሆነ ማህበረሰብ**
   በኖርዌይ ውስጥ እስከ ሽምግልና ጊዜ ድረስ መቆየት ስጋት የሌለው እና አመቺ መሆን አለበት። KrF በቤተሰቦቻቸው ውስጥ የሚገኙ አረጋውያንን የሚንከባከቡ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ መበረታታት አለባቸው ብሎ ያምናል። ስለዚህ KrF ለነዚህ ሰዎች የተለየ ድጋፍ እንዲኖር ይፈልጋል። የአረጋውያን መንከባከቢያ ቦታዎች መስፋፋት እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ አገልግሎት መጠናከር አለበት።

4. **የሰው ልጆች ክብር በሁሉም የሕይወት ደረጃዎች**
   ሁሉም ሰው እኩል ነው። በሁሉም የሕይወት ደረጃዎች ለሰብዓዊ ክብር እንታገላለን። ማንም ሰው መገለል የለበትም! KrF ልዩ ፍላጎት ላላቸው ልጆች የተሻለ ድጋፍ እንዲኖር ይፈልጋል። በማህፀን ውስጥ ላሉ ገና ላልተወለዱ ልጆች እየተደረገ ያለውን አነስተኛ የህግ ከለላ አጥብቀን እንቃወማለን። ለያንዳንዱ የልብ ምት መታገል ይገባናል።

5. **ኢንዱስትሪ እና ስራ የፈጠራ**
   በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች ከስራ ውጪ ሆነዋል። KrF ብዙ ሰዋችን ወደ ስራ ለመመለስ ይሰራል። በተከሰተው ወረርሽኝ ምክኒያት ብዙ ቤተሰቦች ስራ አጥ አና ከስራ ገበታቸው ተቀንሰዋል። ሰዎችን ወደ ሥራ መመለስ አለብን ።


6. **በጣም ከተቸገሩት ጎን መቆም**
   KrF በህብረተሰቡ ውስጥ ይበልጥ ከሚገለሉ ሰዎች ጎን ይቆማል። በአደገኛ ዕጽ ውስጥ ላሉ እንክብካቤን የሚሰጡ፣ በልጆች እና ወጣቶች ሥራ ለተሰማሩ ለትርፍ የማይሰሩ እና በጎ ፈቃደኛ ሰራተኞችን እንደግፋለን። እነዚህ ግለሰቦች ተጠቂ የሆኑ ሰዎችን ለመከላከል እና ለመርዳት አስፈላጊ ናቸው።

7. **ጥሩ ሽግግር ከመዋለ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት**
   ጥሩ የትምህርት ቤት ጅማሪ በልጆቹ ሕይወት ውስጥ ዘለቄታ ያለው እና ጥሩ መሰረትን ይጥላል። በትምህርት ቤት እና በመዋለ ሕጻናት ውስጥ በበለጠ እምነት የሚጣልባቸው በርካታ አዋቂዎችን ይፈልጋል። የመጀመሪያውን የትምህርት ዓመት ጨዋታ፣ ደህንነት እና እርስ በእርስ ግንኙነት ቁልፍ ሚና በሚጫወቱበት የቅድመ ትምህርት ክፍል መተካት እንፈልጋለን።

8. **ህይወት ያለው የአካባቢ ማህበረሰብ**
   KrF መላ ሀገሪቱን መጠቀም ይፈልጋል! የምግብ ምርት እንዲጨምር፣ አርሶ አደሮች የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ እና በተሻለ የእርሻ መሬትን ጥበቃ ማጠናከር የሚያስችል ሁለንተናዊ የግብርና ሥራ እንፈልጋለን። ይህ በመላ አገሪቱ የሥራ ዕድል ይሰጠናል። KrF አስተማማኝ መንገዶችን እና በደንብ የዳበረ የባቡር መስመርን መዘርጋት ይፈልጋል። በሀገሪቷ የተሻለ የህዝብ መጓጓዣ መፍትሄዎችን እና የብሮድባንድ ተደራሽነትን ማሻሻልም እንፈልጋለን።

9. **ኃላፊነት የሚሰማው የአየር ንብረት ፖሊሲ**
   KrF ከዚህ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ምድሪቱን መንከባከብ ይፈልጋል። የአየር ንብረት ቀውስ በመጀመሪያ ደረጃ በዓለም ላይ ላሉት ድሆች ቀውስ ነው። ሰለዚህም ሰዎች ለመሸሽ ይገደዳሉ ፣ እኛም የመርዳት ኃላፊነት አለብን። የአገር ውስጥ ልቀትን በመቀነስ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በንቃት ድጋፍ በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲቆም አስተዋጽኦ ማድረግ አለብን።

10. **እርዳታ ወሰን የለውም**
    ለራሳችን ብቻ እያሰብን መኖር የለብንም! በዓለም ላይ ያሉ ድሆችን እና የተገፉ ሰዎችን የመርዳት ኃላፊነት አለብን። KrF ለነዚህ ሰዎች የበለጠ ዕርዳታ እና ፈንድ እንዲኖር መደረጉ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ እንደሚያመጣ ያምናል!







Amharisk